ከርቀት ሰማ ። ብርዱና በየማሩ ላይ የተጋገረው ጤዛ
ታየውና ስለእነሱ ሰቀጠጠው ።

ከቤቱ ጀርባ ከአጥሩ በመለስ ጥርምስምስ ፤ ችምችም
ካሉት መንደሮች እየተወረወረ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጐላና
እየበረከተ ፤ ዓይነቱ እየበዛ የሚመጣው የሰዎች ድምፅ
ዐይነ ህሊናውን ሳበው ። ወግ ፤ ባህልና ሃይማኖት የተከ
ሉትን ልማድ ለማድረስ በቀዝቃዛ ውሀ ሲነከሩ ጫጫታ
ቸው ብሂላቸው ቁልጭ ብሎ ይሰማው ጀመር ። “ ዋጪው”
“ዋጠው” “ አንድ ጉርሻ ልድገምህ ፤ በሞቴ አፈር ስሆን”
እከሌ ና ቅመስ . . . ይቺን ጉረሳት . . . በሎሚ ውሀ
በፌጦ ድቁስ የተፈተፈተ እንጀራ ሲጐራረሱ የሚቀባበ
ሉት ቃል እየተሰማው እሱም በልጅነቱ ዘመኑ ሲያደርግ
የነበረውን የእንቁጣጣሽ ማለዳ ወግ አስታወሰ ። በከተ
ማው ኑሮ በቤት አካባቢ ቢሆንም በገጠሩ ወደ ወንዝ
ወርዶ ገላን ተለቃልቆ እንደሚመጣም ያውቃል ።
ልማዱንም ኅብረተሰቡንም ታዘበው ። “ ቢልላቸው ኪመ
ጋኛው ፤ ከውጋቱ ፤ ከቁርጥማቱ ፤ ኬቶስቦው ለዓመት የሚ
ያገለግል መከላከያ መውሰዳቸው ነው” ብሎ እያዘነም
በድርጊቱ አፌዘ ። ትዝብቱንም በመቀጠል ፤ “ ወይ ደሀ”
አለ ። “ ወይ ደሃ ካለው ይልቅ ለመኖር የሚንገበገበው
እሱ ነው ። ያጣ የነጣው ሕይወቱ አንድ ቀን በተአምር
በረከት ወርዶለት ይሻሻላል በሚል የንጉሡን ቃል የሹ
ማምንቶቹን ቃል እያነበነበ በተስፋ እንዳንጋጠጠ ከኑሮው
የተሻለ ሞት ይገላግለዋል ። ምንስ አየ ፤ ምንስ አያለሁ
ብሎ በተስፋ ያላዝናል አድሮ መድቀቅ እያሟሟው ፤ አለ
ደሀና ድኅነት ከረፉት ። ወደ ውጭ መስማቱን አቋርጦ
ከግራ ጐኑ ወደ ቀኝ ጐኑ ተገላብጦ ተኛ ።

“ ኤጭ ምን አገባኝ ደሀ በድኅነቱ ውስጥ የሚያበረታ
ነገር ቢያገኝ እንጂ ሌላው ቢቀር ራሱን መገላገል አያቅ

ተውም ነበር ። የሚገርመኝ በዚሁ ኑሮ ውስጥ መተሳሰቡ ፣
መተዛዘኑ ፤ እርስ በእርስ መደጋገፉ ፤ ራስ በራስ መዋለዱ
ነው ። ምናልባት ፍቅርም እነሱ ዘንድ ትኖር ይሆናል ።”
አለና ደሀና ኑሮውን ታዘበ ። ከግቢው በስተጀርባ በቁ
ራጭ ቆርቆሮዎች ተወታትፎ ፤ በቅርጫቱም በሰሌኑም
ግድግዳ ተከፋፍሎ ፤ እጅግ በርካታ ሕዝብ የሚተራመስ
በት ቆሻሻ ሰፈር ሕይወትና ገመናው እየታየው ፤ ሕሊናው
ግን መልሶ እየታዘበው ፤ ምላሱ ሲያወናጭፋቸው የነበሩት
የወገናዊነት ቃላት መልሰው እየጠዘጠዙት ሰላም አሳ
ጡት ። እንደገና በጀርባው ተንጋሎ ተሸፋፍኖ ተኛ ።

ከራሱ መሸሽ አልቻለምና የሕሊናውን ጭውውት
የግድ ማድመጥ ነበረበት ። ቀስ በቀስ እየጠራና እየ
በረታ የሚደቀንበትን ትርኢት ያይ ጀመረ ። ራሱን በ
ራሱ ውስጥ ከልጅነት እስከ ጉርምስና ከዚያም ጉልምስና
ዘመኑ ውስጥ አሾተዋለው ። ያለፈበት ጐዳና ከጅምሩ በች
ግር የተሟሸ ነበርና ጭንቀትና ጥረቱን የተስፋ ሕልሙን
አሳምሮ አስታወሰው ። ከድኅነት ማጥ ሊወጣ በታገለ
በት መራራ ጊዜው ዓላማ አድርጐ የተራመደው ለብዙ
ሀን ድሆች አርነት ጭምር ሊታገል ወስኖም ነበር ።
ስለ ድሆች መመዝበርና መጨቆን ፤ መናገር ኃጢአት በሆ
ነበት ወቅት ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ተናግሮላቸዋል ።
ብልጣ ብልጥ አፈኞች በክብርና በሥልጣን ቁንጮ ላይ
ተፈናጠው ኃይል ተጐናጽፈው ሲመዘብሯቸው ለአገ
ዛዝ ለአስተዳደር የተመረጡ ፤ የተቀቡ መሆናቸውን በኅ
ብረተሰቡ ሕሊና ውስጥ በግድ እያሰረጹ እድሜያቸውን
ሊያራዝሙ ዘራቸውን ሊያበረክቱ ሥልጣን ከጃቸው እን
ዳትወጣ ልዑላን መሳፍንት መኳንንትን ሲያበራክቱ መደ
ርጀታቸው ሀቅ ቢሆንም ሥሩ የበሰበሰና ሕዝብ የጠላው
የጭቆና አገዛዝ በቀላሉ የሚናድ መሆኑን የተገነዘበው መቼ

CS CamScanner

እንደ ነበር ሲያስታውስ የልጅነት የፍላት ስሜቱን አደ ነቀው ። ሆኖም ቃሉ ቃል አልሆነም ። የሰጠውን ቃል የትግል አጋርነት መሀላውን ባንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ በላው ። የደሀ ሥቃዩና ገመናው ከረፋው ።

“ እስኪነክስ ያገኑነብስ ” አለ ። የአውሬነት ባህሪውን የሕሊናው ትዝብት እየተጠየፈው ። ያለበትን የኑሮ ደረ ጃ ፤ ጥቅሙንና ክብሩን እየመዘነ ፤ ወትሮ ሲኮንናቸው ከነበሩት ከአጼው ባለሟሎች ተመሳስሎና ተስተካክሎ ሌላ ደም መጣጭ በመሆኑ እፍረት ተሰማው ። “ ሺት ” አለና ያደረ ምራቁን ተፋ ።

በት/ቤት ሕይወቱ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለ በት/ቤቱ የተማሪዎች ምክር ቤት ተመራጭና ተደማጭ ሆኖ ያሳለፈ ውን ጊዜ ገላልጦ አስተዋለው ። “እኮ” አለ ቁጣ እየወረረው እኮ ያኔ በት/ቤት በተማሪዎች ምክር ቤት አንድነታችንና እንቅስቃሴያችን የኢትዮጵያን ሕዝብ ከምዝብርነት ከገ ባርነት ለማላቀቅ ፤ የሀሰት ልባስ የተከናነበውን የአገዛዝ ሰንሰለት ግልጥልጥ አድርገን አሳይተነው ፤ ጠላቱን አውቆ ለትንቅንቁ እንዲጠነክር ልናነቃው ለትግሉ የፊት መሪ ሆነን ልንዋደቅለት ነበር ። ቃላችንን ያፈሰስንበት መድ ረክ የቀባጠርንበት መድረክ ብዙ ነበር ። ቃላቸውን ያላ ጠፉ ፤ ፊት ለፊት የተጋፈጡ በእስር ቤት ሥቃይ ፤ በክ ብር ዘበኛ ዱላ እየተቀጠፉ ቢሞቱም ከህሊናቸው ደስታና ጠንካራ አቋም ጋር በጀግንነት አልፈዋል ። ሆኖም ሙጃ በቅሎባቸዋል ። ሙጃው ተመንጥሮ አጥንታቸው ተሰባ ስቦ እውነተኛ ዜጎች የሚገባቸውን በሕይወታቸው ላፈ ሩት የትግል ክብር መታሰቢያ የሚሆን ሀውልትና ቅስት ይተካበታል ። እኔ ግን አፌን ለጉሜ አወጣጤን አስ ልቼ አቀማመጤን አሳምሬ ደሀውን እያጣጣምኩ በመም ጠጥ ላይ እገኛለሁ ። ታዲያ ደሀው ለምን አይደኸይ ፤ለምን

አይቆረቁዝ ፤ ሲጎርስ የኖረው ተስፋ ፤ እናጉርስህ ብለን ስናደነቁረው የኖርነው ተስፋ ፤ የማይቆረጠም ወርቃማ ቃላት ፤ አንጀት የማይደግፍ ወገናዊነት ፤ ድንቄም ትም ህርት ድንቄም መቆርቆር ” አለ ። የተማረው ትምህርት ከምን ላይ እንዳበቃ ገምግሞ ።

ረጋ ብሎ ስሜት እየፈነቀለው ያደርገው የነበረውን የን ግግር ስልት አስታውሶ ፤ ደሀውን ብሶቱን እየደነቆለ ፍላጎቱን እያስተጋባ ፤ የብልጽግና ሕይወት ሊመሠርት ለት ፤ በቋንቋው በደሀ ፈሊጡ ፤ በዚህ እድሜውና ደረ ጃው እንደጉም በበነነው ትረካው ሲቀደድለት ፤ ሕዝቡ በምኞት በጉጉት ያደምጠው ያምነው ይተማመነው እንደ ነበር የህሊናው ትርኢት እያሳየው አዘነ ። የሕዝቡን ቆራ ጥነትና ጀግንነት ቢያውቅም በእርጋታውና በአማኝነቱ እያደነቀው በራሱ ቅጥፈት ግን አፍሮ ከሕሊናው ስር አቀ ረቀረ ። በሰላ ምላስ የሚወነጨፉ ቃላትን ግላዊ ዓላማ ያሸመቁና ብሔራዊ ስሜት ተላብሰው የሚምዘገዘጉ ቅጥ ፈቶች ያዳመጠ ሕዝብ ፤ በቋንቋው በፈሊጡ በብሶቱ በስሜቱ የሚያስመስሉትን ሁሉ ይገመግማል ። አለ ። ሂደቱንም ገምቶ ውጤቱንም መዝኖ ሲቀልበት ይጠየፋል ። አቅም ስለሌለውም እስከዚያው ፍቅሩን ይነፍጋል ። የተነ ሣለት ግን ይደመስሳል ። ወየው ግን ይህ ደሀ ሁሉ የተነሣ ዕለት ብሎ ተከዘ ። የፓርላማ ተመራጭ ሊሆን ልቡ ከጅሎ ያንኑ ሕዝብ ሊያታልል ያቀደበትን ሁኔታ አስታውሶ ፀፀ ተው ። ያኔ አስታኮ ያስተጋባው የግል ፍላጎቱን እንደነ በረና ያነጣጠረውም ለግል ምቾቱ እንደነበር አረጋግጦ ደሀና ድኅነት ትግልና ነጻነት እንደተረሱት ሆን ብሎም እንደረሳቸው አሰላስሎ በቅሬታ ተወጋ ።

“ ሺት ” አለ እንደ ልማዱ ። ጥቂት ቆየና ራሱን ማጽናናት ፈልጎ ቀስ በቀስ ወደ ሌላኛው ሀሳቡ አዘነበለ ። “ አንድ

እጅ እያጨበጭብ . . . አንድ እንጨት አይነድ ምን
ላድርግ ” አለ ። ወዲያው ከት ብሎ በነገሩ ሣቀ ። ራስን
ማታለል ምንኛ አዳጋች መሆኑን አውቆት ነው ። ማሰላ
ሰሉ ሰለቸውና ተነጫነጨ ። የግድ ራሱን ማጽናናት እን
ዳለበት ወስኖ ፤ “ ኤጭ እኔ ብቻዬን የበደልኩት ደሀ
የለ ። ሁሉም በደሀ ስም ሲያላዝን ሰንብቶ ቂጡን ከመ
ቀመጫ ሲያደላድል ይተፋዋል ። ይጠየፈዋል ። እያን
ዳንዱ ደሀ ዕድል ቢደርሰው ከኔ የተለየ አያደርግም ።
ደግሞስ ብዙ ግፍ ተግቶ ፤በብዙ ትግል ደምቶ ፤ ገና ተግጦ
ቶመላልጦ ለሚያልፍለት ሕዝብ የኔ መንጨርጨር ብቻ
ውን ምን ይፈይዳል ፤ እንደ ብረት ሰንሰለት የተጠላለ
ፈው የንጉሡ አገዛዝ የሚበጠስበት የተባበረ ጉልበት እስኪ
ሰበሰብ ገና የት የለሌ ነው ። አቦ የራሱ ጉዳዩ አለ ። ያፉ
ንም የሕሊናውንም ምሬት የያዘ ምራቁን ወደ መሬት ቲፋ።

ሁለት እጆቹን አጣምሮ ለጭንቅላቱ አንተርሶ ጭልጥ
ብሎ ወደ ጀመረው የሀሳብ አዘቅት ወረደ ። በዚህ ሀሳቡ
ኅብረተሰቡን የጊዜውን ወጣት ትውልድ ቃኘ ። ወጣቱስ
ትውልድ እንደእሱው ወኔው ሸንቶ እንደሆነ ወይም የቀጠነ
እጥብጣቢ ቢጤ በውስጡ ይፈስ እንደሆነ ለማወቅ ግም
ቶችን ጣለ ። ሁለቱን ከንፈሮቹን ወደ አፍንጫው ሰብስቦ
ትውልዱን በትዝብት አሸተተው ። የዘመኑን ወጣት ፤
ተተኪውን ትውልድ ገረመመው ። እንኳን ጠላቱን ወዳ
ጁን ለይቶ የማያውቅ ቂላቂል ስብስብ ብሎ ናቀው ።
እንደ ልፈፋ ጽድቅ የንጉሡን የልደት ዜማ የንግሥ በዓል
ቀረርቶ ከማድመቅ ከማዳነቅ ወዲያ መለስ ብሎ ታሪኩን
ዝቅ ብሎ መሠረቱን የማያይ የጋሪ ፈረስ ብሎ ታዘበው።
የባለ ሥልጣን የባለ ጸጋው ልጅ ባገር ውስጥ በምርጥ
ት/ ቤት ፤ ካልሆነም ዶላር በሚፈስበት የውጭ ትምህርት
ይቀረጻል ። ይታነጻል ። ግላዊ ምቾት ግላዊ ደስታ ሲሞቅ

ያደገ የጥቂት ባለሥልጣን ልጅ ሁሉ ለግል ምቾቱ እንደ
ማሰነ ያልፋል ። በችግር እየደቀቀ ከህመም እየታገለ መሳሳ
ሰላላ ፤ ጐባጣ መጣጣ ሆኖ ያደገውም ደሀ እድገቱ የሚያ
ነጣጥርበት ነጥብ ያው ለግል ሕይወት መሟላትና መስ
ተካከል የሚውል መሆኑን ገመተ ። ዓለም ሲፈጠር እንደ
ነበረች ያለችው የአበሻ ምድር ለተናጠል ጥቅም በሚሯ
ሯጡ ዜጐችዋ እንደተረገጠች ለብቃትዋ ትደርሳለች ብሎ
ገመተ ። የወኔውን ነገር ግን በውስጡም ፈተሸ ። የያኔው
የወገን ፍቅር የያኔው የትግል ግለት ፣ የያኔው ዓላማ አጠ
ባበቅ በዚህ እድሜና ደረጃው በውስጡ ጅንጥፍጣፊ ትቶ
እንደሆነ አካሉንም ነፍሱንም በዐይነ ህሊናው ዳሰሰው።
ይኑር አይኑር አላወቀውም ። የህሊናው ንትርክ ሰለቸው፤
የለበሰውን የሌሊት ልብስ በንዴት ገልቦ ተነሳ ። እየተግ
ተረተረ ዐይኖቹን እያሻሸ ወደ ሳሎን ወጣ ። የመስኮቱን
መጋረጃ ወደ ጐን ሰብስቦ መስኮቱን ከፈተው ። ቀዝ
ቃዛው የመስከረም አየር ተኽርገድጉዶ ገባ ። ባፉም ባፍ
ንጫውም ወደ ውስጡ ማገው ። እጆቹን አጣምሮ በመስ
ኮቱ ጠርዝ አስደግፎ የውጭውን እንቅስቃሴ መመልከት
ጀመረ ። በመስኮቱ መዝለቁን ያዩ ሕጻናት እየተሯሯጡ
መጥተው ከፊቱ ፈሰሱ ። እጅግም በእድሜ የማይበላለጡ
ሴት ልጆች ከበሮአቸውን እየደለቁ ፤

ሆ ብዬ መጣሁ ሆ ብዬ
ጌቶች አሉ ብዬ
አበባየሁ ሆይ

ለምለም . . . አበባየሁ ሆይ . . . እያሉ አንጋጠው
እየተመለከቱት ዝማሬያቸውን ቀጠሉ ። ተራ በተራ
ተመለከታቸው ። ብርዱን ለመቋቋም አንገታቸውን በት
ከሻቸው መካከል ለመቅበር የሚሞክሩ አሉበት ። የሚ
ያጨበጭቡበት እጃቸው በቆፈን ተንጨፍሮ ሰውነታቸው

CamScanner

በተለይም ከንፈራቸው የሚንቀጠቀጥ አየ ። ከሥር ከለ
በሱት ማሰሻ ከሚመስል ቡቱቶ ላይ ከተለያዩ ቁርጥራጭ
አዲስ ጨርቅ አስተዋጽኦ የተሰፋ አዲስ ጥብቆ የለበሱ
አልፎ አልፎ ከመካከላቸው ተመለከተ ። ግማሹ ትኩስ
ልጩ መላጣ ፤ ግማሹ የቅጫም ሰንሰለት በጭንቅላቱ ዙሪያ
የተጠመጠመበትና የወጉን ቅቤ በዚያው ላይ የለጠፈ ነበር ።

ከውስጡ አንዳች እሳት ሲያንሠራራ ተሰማው ።
“ ሺት ” አለ ። ግንባሩን አጨማዶ በክፉ ፊቱ ልጆቹን
በጥላቻ ገርምሞ መስኮቱን በኃይል ዘግቶት ተመለሰ ።
ልጆቹም በሁኔታው እየተገረሙ እየሳቁ እየተንጫጩ ወደ
ሌላው ቤት ደጃፍ ከበሮአቸውን እያሚሹ ሮጡ ።

የዕለቱን ወግ ተከትሎ እንደሰው እደጅ ወጥቶ ባይ
ለቃለቅም ፤ ውብሸት በመታጠቢያ ክፍሉ ገላውን ታጥቦ
ጺሙን ተላጭቶ የክት ልብሱን ለባበሰ ። መታጠቢያ ቤት
እንደነበረ የገባችው ተመላላሽ ሠራተኛው በምታቁላላው
የወጥ ቁሌት የቤቱን ጠረን ስለለወጠችው ራበው ። መጠጥ
የቦረቦረው አንጀቱ አፍ አውጥቶ ተጣራ ። ታጥቦ ሲወጣ
“እንኳን አደረሰዎት” ጋሼ አለችው ። ቀና ሳትል የያዘ
ችውን ቁርስ ከጠረጴዛው ላይ እያደላደለች ። “ እንኳን
አብሮ አደረሰን ” አላት ዐይኑ ምግቡን እየተከተለ ።

ውብሸት ቁርሱን እስኪበላ የተመሰቃቀለ መኝታውን
አንጥፋ ፤ ነገር ሲያባዝት የተፋውን ጠራርጋ መስኮት
ከፍታ ፤ ንጹህ አየር አስገብታ ወደ ሥራዋ ተመለሰች።
በጠይም ቆንጆ ገጽታው ላይ የራሱን ማስተካከያ ጨም
ሮበት ጠረኑን በሽቶ አጣፍጦ ከምንጊዜውም ቀውቦ
ቁርጥ ያለ ሰዓት ያልሰጠችውን ፍቅረኛውን ፤ እጮኛውን፤
አበባየሁን ፤ለመጠበቅ ተሰናዳ ። የማታ ማታ የደወለችው
የታየች አባ ጨፍቅ ነገር ግን ሰላም አልሰጠው አለ ። በዕ

ለተ እንቁጣጣሽ በቡና ቤቷ በርካታ ሰዎችን መቀበልና
ማስተናገድ ስላለባት የንግዱ መድራት ሊያደርሳት ይች
ላል ፤ የሚለው ሀሳቡ ቢያጽናናውም ጥርጣሬው ሲገነ
ትለው ደግሞ ፤ የሴት ነገር አይታመንም ለተንኮል ብላ
ድንገት መጥታ ትበጠብጠኝ ይሆናል ያሰኘው ጀመር ።
ሲሆን ማታ አለበለዚያም አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ እን
ድትመጣ ተመኝቶ ራሱን ለዕለቱ ሁኔታ አዘጋጅቶ ተሰ
ናዳ ።

በረጅም ቁመናው የተደላደለው ሰውነቱ ልብስ ይቀ
በላል ። ደመናውን ገፍታ ቆይታ ቆይታ የወጣችውን የም
ስራቅ ጸሐይ ለመሞቅ ወደ ደጅ ወጥቶ እግሮቹን አንፈራጦ
ቆመ ። በቤቱ ፊት ለፊት ያስተከላቸውን ለጋ የጽድ ችግ
ኞች እያየ ረጅም አፍንጫውን ማሻሸት ጀመረ ። ዐመል
ሆኖበት ጉድፍ የሌለበትን አፍንጫውን አሁንም አሁንም
መዳበስ ይወዳል ።

የሳሎኑን በር በመጠኑ ከፈት አድርጋ “ ጋሽ ” አለ
ችው በሰለለ ድምጿ ፤

“ ምነው ”

“ ዶሮ የሚያርድልኝ አጣሁ አንድ ጊዜ እረዱልኝ”

“ ዘበኛውን ፈልጊና አሳርጅ ”

“ አጣኋቸው”

ደስ ሳይለው ተከትሏት ገባ ። አርዶ ሲመለስ የሠራ
ተኛው የራስ ቅቤ ገማውና አፍንጫውን ማሸት ቀጠለ ።
ኋላም መሀረሙን አውጥቶ አሸተተውና ተገላገለ ። ሰፊ
መስተዋት ያለውን የእንግዳ መቀበያ ክፍሉን ሙሉ በሙሉ
ብርሃን እንዲገባበት መጋረጃውን ሰበሰበው ። ብዙ ጊዜ
ተከፍቶና ሽክላ ተጫውቶበት የማያውቀውን ሬዲዮ ግራ

CamScanner

ማፎን አየት አድርጐ ፈገግ አለ ። ከላዩ ላይ ያሉትን የጌጥ
ጥቃቅን እቃዎች አንስቶ ከነባር ሸክላዎቹ መካከል የጂ
ምሪቭዝን ኢን ዘ ሚስቲ ሙን ላይት መርጦ እንዲዘፍን
አደረገ ። ዜማውን የዘፋኙን ድምጽና ሐኑታ እያዳመጠ
ከወዲያ ወዲህ እየተንጐራደደ ሣቀ ። “ ፍቅር ያለ ጥቅም
አይሞቅም አይደምቅም ወዳጄ ፤ የፈረንጅ ጅል ” አለ
ሸክላው ዘፈኑን ሲያበቃ ። አንዴ አንገቱን በመስኮት ብቅ
ቶያደረገ ውጭውን እየቃኘ ፤ አንዳንዴም የእግር ኮቴ እያ
ዳመጠ እየተንጐራደደ ነበር ሸክላዎቹን በተከፈለ ልብ
ያዳመጣቸው ።

መሉል ባለው ቁመናዋ ሙሉ በጥልፍ የተንቆጠቆጠ
ነጭ ሸማ ለብሳለች ። በተንቀሳቀሰች ቁጥር የእርምጃ
ዋን ስልት እየጠበቁ የሚቦርቁት ጡቶችዋ ለቀቅ ባለው
ሸማ ውስጥ የደረትዋ ሜዳ የጠበባቸው ይመስላል ።
የደረትዋ ሙላትና ጥራት ከአንገትዋ አወጣጥ ጋር ከሸ
ማው ደምቆ ይታያል ። በጣቶችዋ ላይ የተደረደሩት የወ
ርቅ ቀለበቶች ይፍለቀለቃሉ ። እንደ ጥርኝ የሽቶዋ መዓዛ
በአለፈችበት መንገድ ላይ ይቀራል ። እንደ ነገሩ ሸብ ያደ
ረገችው ሻሽ አስተሳሰሯ አሳምሯታል ። ከተፈጥሮ ቀለመ
መልካም የሆነው ከንፈሯ ገጠም ስታደርገው የጽጌረዳ
እንቡጥ ይመስላል ። ትናንሽ ዓይኖቿ በደመቀ ኩል ታጥ
ረው ከግንባሯ ሥር ያበራሉ ። አመለካከቷ ማባበልም
ትህትናም ትዝብትም ያቀላቀለ በመሆኑ ቀና ብላ ያየችው
ሁሉ ሲሸበር ታየዋለች ። በጭውውትም ሆነ በንግግሯ
ወቅት ፈልፍለው የሚያዩት ትናንሽ ዓይኖችዋ አልፈው
ውስጣዊ ሁኔታን ማንበብ የሚችሉ ይመስላሉ ። ወንዶች
እየወደዱ ይፈሯታል ። አንደበትዋ ሳቅዋ የተቆጠበ በመ
ሆኑም ትከበራለች ።

ታየች አባጨፍቅ በከፍተኛ ገንዘብ የሚገመት ቡና
ቤት ያላት በሥራ በርካታ ወጣት ሴቶችን የምታስተዳድር
ከነሙያዋ ጐልታ የምትታይ ሴትኛ አዳሪ ናት ።

ነጭ አራት መቶ አራት ፔጆ መኪናዋን እያሽከረከ
ረች ከውብሸት እንዳይላሉ ሰፈር ስትደርስ ጊዜው ሰባት
ሰዓት ሆኗል ። የመኪናዋን ቁልፍ በጣቶችዋ ላይ እያሽከ
ረከረች ሳብ ረገብ በሚል አካሄዷ ከበረንዳው ደርሳ በሩን
ስታንኳኳ ፈገግታው በፊቱ ላይ እንደ ደመቀ ውብሸት
እንዳይላሉ ፈጥኖ ከፈተላት ። ሆኖም ሲያያት በመደንገጡ
ለወትሮው የሚያደርገው የሚናገረው ሁሉ ጠፍቶበት
ቆሞ ቀረ ። ፈገግታውን ድንጋጤው ከመቅጽበት ሰለበበት።
ገፍታው ገባች ።

“ የታሉ ዘመዶችህ ? እንኳን ቤተዘመድ የዋለበትና
ያደረበት ፤ ሰው የረገጠው አይመስልም ቤትህ ” አለችው
የጐሪጥ እየተመለከተች ፤

“ አሁን ወጡ ታዩ ፤ እኔም ወዳንቺ ልመጣ ስነሳ
ነው የደረስሽው ”

“ ዋሾ ሰው እንቃለሁ አትዋሽብኝ ”

“ ታየች እመቤቴ ሙች ፤ ከሄዱ ፤ ከወጡ በኋላ
ተጠራርገው ቂጠማ ተበትኖ አይተሽ ነው እንጂ በባላገር
ኮተት ቤቱን መላ አሳጥተውት ነበር ”

“ ነው ?” አለችው በእኒያ ዐይኖችዋ ቁመናውን ከቃ
ኘች በኋላ ቀዝቀዝ ባለው አስተያየቷ አጠንክራ እየተመ
ለከተችው

“ ዛሬ ደሞ እንቁጣጣሽን ራሷን መስለሻል የት ኖሯል
የደበቅሽው ”

CamScanner

" ምኑን "

" ይኸን ሁሉ ቁንጅና "

" ዐይንህ ብዙ ስለሚያይ አላስተዋለውም እንጅ ያለኝ አብሮኝ የኖረ ነው" ንግግሯ ቧጠጠው ራሱን አሰባ ሰበና ሌሌላ ነገር ያሞጠሞጠ አፏን በአፉ ሸፈነው ።

በአንድ እጇ ወገቧን አቅፎ በአንድ እጇ ፊቷን ከፊቱ አስጠግቶ ይዞ እየሳማት ቀስ በቀስ አቀለጣት ። እንደምንም ራስዋን አስለቅቃ ፤" እኔ ቤት ልትመጣ በዝግጅት ላይ ከነበርክ እንሂድ ፤ ቤትህ በጣም ቀዝቅዟል " አለችው የረ ጅም አፍንጫወን ጫፍ እየሳመች ፤

" ከመጣሽማ የናፈቅሁሽን ያህል አገኘሁሽ ወደ ሌላው ፕሮግራም እሄዳለሁ "

" ምን የሚሉት ፕሮግራም "

" የነበረኝ ፕሮግራም አንቺ ቤት በቁሚ ደርሼ እና ቴና አጐቴ ወደ ሄዱበት ሌላው አጐቴ ቤት መሄድ ነበር"

" እውነትም ተወጥረሃል ፤ ቸኩለሃላ? " አሽሟጠ ጠችው ፤

" ታዬች ሙች ሳላይሽ ስላደርኩ ጨንቆኝ ላይሽ ፈልጌ ነው ከነሱ ተነጥዬ የቀረሁት እንጂ መሄድ አለብኝ"

" ነው እንዴ " እንደ መንጋለል ብላ ከት ብላ ሣቀች ጭንቅላትዋን መለስ ስታደርገው ቱቀብሎ ኪናፍርዋን መጠጣቸው ። ቲቃቅፈው እንደ ቆሙ የሳሎኑ በር ተን ኳኳ ።

ከመቅጽበት ያቀፈውን ወገብ ለቆ ፈጥኖ ከሶፋው ላይ ተስተካክሎ ተቀመጠ ። ታየች አባ ጨፍቅም እየተነ

ሰነሰች ወደ መኝታ ክፍሉ ገባች ። ኳኳታው ተደገመ ። ውዴ ከወጥ ቤት መጥታ በር ከፈተች ።

ገና በመፈንዳት ላይ ያሉና ፈንድተው ቀለማቸውና መዓዛቸው የሚስብ ጽጌረዳዎች ይዛ እሷም እንደ ጽጌረዳ ፈክታ ስትገባ ውብሸት ከተቀመጠበት አልተነቃነቀም ።

" እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሰህ "

" እንኳን አብሮ አደረሰን " አላት ።

ከተቀመጠበት የጋለ ግንባሩን ስማ ፤ ያመጣቻቸውን አበ ቦች ከማስቀመጫው ውስጥ ለማድረግ አልፋው ጥግ ይዛ ወደ ተቀመጠችው ጠረጴዛ ተራመደች ። በተለያዩ አቅጣ ጫዎች እያዘነበለች ፤ ከፍና ዝቅ በማድረግ በይበልጥ ዐይን እንዲስቡና ውበታቸው ይፋ እንዲታይ ጥበብ ባለው ሁኔታ አበቦቹን በማስቀመጫው ውስጥ ካስተካከለች በኋላ ውዴን ጠርታ ውሀ አስመጥታ ጨመረችበት ። ማሰማ መሩን ካበቃች በኋላም በፈገግታ እንደደመቀች ዞራ ብት መለከተው ከነበረበት ሳይነቃነቅ ፊቱ ጠቁሮ ተመለከ ተችው ። ከወትሮ ሁኔታው እጅግ ተለየባት ።እየጨነቃት ተገረመች ።

" ምነው ውብሸት የተከፋህ ፤ የተረበሽክ ትመስላለህ አመመህ ወይስ በመምጣቴ ቅር ተሰኘህ "

" አይ አይደለም "

" ሁኔታህ ግን ችግር እንዳለብህ ይናገራል "

" መስሎሽ ይሆናል ፤ እኔ ግን ደህና ነኝ "

" ዋናው ደኅንነትህ ነው" ብላ ከሶፋው ላይ አረፍ አለች ። ፊት ለፊት ተቀምጣ በትኩረት ተመለከተችው። ጤናማ ስሜት እንደ ሌለው ተረዳች ። ቀና ብሎ ሊያያት አል

CamScanner

ቻለም ። አልፈለገምም ። ከተቀመጠበት ተነስቶ እጆቹን ከኪሱ ከቶ ጀርባውን ሰጥቷት ሲቆም ከመቼውም የበለጠ የገዘፈ መስላት ። ከበድ ያለ ጭንቅላቱ ፤ ሰፋ ያለው ትከሻው ፤ ሞላ ያሉት ጭኖቹ ፈርጠም ያሉት ባቶቹ ዠርገድ ካለው ቁመናው ጋር ዐይኖቿ የሚወዱት ተፈጥሮው ነው ። እንደሌላው ቀን ቢሆን ኖሮ ፤ እንዲህ ብሎ ሲቆም ከኋላው ወገቡን አቅፋ ፤ በጸጉር የተላበሰ ጭንቅላቷን ከትከሻው ዝቅ ከወገቡ ከፍ ባለው አካሉ ላይ አስደግፋ ታሻሸው ነበር ። በዚህ ሁኔታው ግን ባላወቀችው ምክንያት ተቆጥቶና አኩርፎ ስላገኘችው እንዲህ ማድረጉ ትዝ አላላትም ።

የመውደድ አቅሏን ያንጠለጠለው ይህ ተፈጥሮው እየነዳ አምጥቶ ከዚህ ሁኔታ ደነቀራት እንጂ ሕሊናማ ቢያት ሰው ሁሉ ሀሳብና ምኞት ውስጥ የምትመላለስ ቆንጆ ናት ። በሕመም ወይም በምግብ እጦት እንደሚደርሰው ሰለል መለል ያለ ሳይሆን ፤ ቅጥነትዋ መጠን ያለውና በቅርጽ ነው ። ከሀሉም ከሁሉም ወገቧ የባሰውን ቀጥና እህል ባንጀትዋ የሚያሳልፍ አይመስልም። ይህ ሁኔታው ታዲያ የዳሌዋን ስፋት ያጋልጠዋል ። ማንም ሰው በአንድ ጊዜ እይታ አያልፋትም ። ታሳሳለች ። ታሳዝናለችም ። የሁሉ ዐይን የሚወድቅባትን ያህል ለሁሉም አትከንፍም ። ከቁመናዋ ፤ ከውበትዋ ባላነሰ መንገድ የሚያስወድዳት ደግሞ ረጋ ያለው ተፈጥሮዋ ነው ። ማንም በተመኛት ማግስት ሊያገኛት የሚችል ስላልሆነች ወዶ የሚናፍቃት ብዙ ነው ።

“ ምን ይደረጋል ” አለች ረዘም ባለ አባባል በውስጧ ታምቆ የቆየውን ቅሬታ ለመተንፈስ ፤

“ ምኑን ” አለ ፊቱን ሳይመልስ

“ የስሜት ሚዛን ሲደፋ ”

“ አልገባኝም ”

“ እንዳንቺም ኮርቻለሁ ፤ እንዲህ እንዳሁኑም ሆኛለሁ ፤ መውደድ ባንዱ ላይ ብቻ ሲያደላ ያ ሰው ሥቃይ ውስጥ መውደቁን እያስተዋልኩት ነው”

“ አንድ ነገር ማስታወስ አለብሽ ” አላት በወሬረድምጹ ላይ ቁጣ ቢጤ ደርቦበት ፤“ ከሰዎች ጋር የምትነጋገሪባቸውን ቃላት ግልጽና ቀላል ማድረግ መቻል አለብሽ ፤ መስቀለኛ ምርመራሽንና ቅኔሽን ፤ በፍርድ ቤትሽ አካባቢ አውይው ። የምትናገሪው እንዲገባኝ ከፈለግሽ በቀላል አማርኛ ማለት የምትፈልጊውን ተናገሪ ”እግሯን እያሻሸች ፤ እሱን ሳይሆን የወለሉን ምንጣፍ አቀርቅራ እየተመለከተች ጥቂት ጊዜ ዝም ካለች በኋላ ቀጠለች።

“ የተሰማኝን ሳልናገር መሄድ አልፈልግም ። የምናገረው ሁሉ እንደ ገባህና ሊገባህም እንደሚችል አውቃለሁ ። ወደድኩሽ ያለኝ ሲንገበገብ የስሜቱ ጠብታ ሳይነካኝ ቀርቶ ሁኔታውን በፌዝ ያየሁበት ጊዜ አለ ። እኔን በተራዬ መውደድ ቃኝቶኝ መውደዴን ችላ ብለሃት ሳይከመገረም ሌላ አላዘንኩም ። ሆኖም አልተገመዳሁም ማለት አልቃጣም ። ምን ይደረግ ፤ ይህን ስሜት በምንም ልትፈጥረው አትችልም ። አዝነህ ፤ ለምነህ ፤ ገዝተህ አታመጣውም ። በይሉኝታም የምትሰጠው ወይም የምትቀበለው አይሆንም ። ፍቅር ራሱን መፍጠር አለበት ። እና ባንተም በእኔም መፍረድ አልቃጣም ። አጋጣሚው መራራ ነው ። ሆኖም ማስመሰል በመቻልህ ባይደንቅህም ልንቅህ ግን ተገድጃለሁ ። ግብዝና ራስህን ወዳድ ነህ ”

“ ሌላ የምታወሪው የለሽም ”

" ሁኔታህ የጋበዘኝን ተናግሬያለሁ ለማንኛውም ደህና ሁን "

በመጣችበት ሁኔታ ሳይሆን አንዳች ነገር ትከሻዋ ላይ እንዳረፈ ሁሉ አንገትዋን አቀርቅራ ወጣች ። እንደ ከዚህ በፊቱ አልሸኛትም ። ሕሊና መሸሻ በሕግ ትምህርት የተመረቀች የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሠራተኛ ነበረች ።

የአጋጣሚዎች ግጭት በፈጠረው ምስቅልቅል መሀል ቆሞ በወረረው ብስጭት የተነሣ የደም ሥሮቹ ፈጠው የሚለው የሚያደርገው ጠፍቶበት በዝምታ በሳሎኑ ውስጥ በመንጐራደድ ላይ እንዳለ ውዴ የቡና ዕቃዋን ሰብስባ ከወጥ ቤቱ ብቅ አለች ። በመኝታ ክፍሉ በአልጋው ሙሉ ተዝናንታ የተንጋለለችው ታየች አባ ጨፍቅም ህሊና መሸሻ ገብታ እስክትወጣ ድረስ የተነጋገሩትን ሁሉ ሰምታ በሁኔታው ተነክታ ነገር ታሰላስል ነበርና እንደ ተጋደመች ቆየች ።

ታየች አባ ጨፍቅ በለጋነትዋ ፤ በየዋህነትዋ ዘመን ያቃጠላት የፍቅር እሳት የፈጠረው ቁስል እያመረቀዘ ስለሚጠዘጥዛት ትሸሸዋለች ። ፍቅር የሚሉት እሳት በሕይወቷ ማላዳ ለቅጽበት ያህል ነዶ ቁስሉን ትቶ ከጠፋ ዓመታት አልፈውታል ። በያዘችው ኑሮዋ ፍቅርን በመሣሪያነቱ ትጠቀምበታለች ። ታስገድድበታለች ። ፍቅርን በስሜቱ ግን ትርቀዋለች ። ይህም በመሆኑ ባደመጠችው ምልልስ አጥብቃ ብትነካም ቅንጣት የቅናት ስሜት አልተፈጠረባትም ። ታየች አባጨፍቅ ዓላማዋ ተጠቃሎ ያተኮረው ገንዘብ በማግኛ ዘዴና ሀሳቦች ላይ ስለሆነ ወደድኩሽ ለሚላት ሁሉ ፈገግታዋን እየቸረች ልቧን ትዘጋበታለች ። በሰማችው ምልልስ ይልቁንም ውብሸት እንዳይላሉን አጥብቃ ናቀችው ። በፍቅር ስሜት ተጐትታ መጥታ ተክዛና መንፈሷ ተሰብሮ የተመለሰችው ሴት አሳዘነቻት ።

ቡናው ሲቆላና ሲሻተት ተጠራችና በሸማዋ ሙሉ አምሮ የሚታየውን ሰውነትዋን እያውረገረገች ወደ ሳሎኑ መጥታ ተቀመጠች ። ምንም ቃል ሳይነጋገሩ ጥቂት ጊዜ አለፈ ። የተቋረጠ ጨዋታቸውን ለመጀመር ሀፍረት ተሰማው ፤ ሁለቱም በልባቸው የግላቸውን ሀሳብ እየፍተለተሉ ዐይናቸው ግን በውዴ የቡና አፈላል ስልት ላይ ተተከለ ። በለምለም ቄጠማው ላይ የፈካ የማሽላ ቆሎ በተን ካደረገች በኋላ እጣኑንና ሰንደሉን አጫጪሳ የቡናውና የጪሳጪሱን ጠረን አምሮት ሲቀሰቅስ ምሳ አቀረበችላቸው ።

ለመጀመሪያ ጊዜ በውብሸት ቤት ውስጥ የተጠመቀ ነው ። የጠላውን ጣዕም የዶሮ ወጥዋን መጣፈጥ እያደነቀች ታየች አባ ጨፍቅ ውዴን ልብ ብላ አስተዋለቻት ። ውቃቢዋ ወደዳት ። ወዲያው ከጀለቻት ። ሙያዋ ልጅነትዋ ትህትናዋ ፤ ቀስ በቀስ የታያት ውብትዋ ሁሉ ሳባት ። ሸጋ ባለሙያ ልጅ አለቻት በልቧ ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላም ዝምታውን ገሠሠችውና ፤

" ሠራተኛህ ባለሙያ ነች ፤ ወጥዋም ጠላዋም ቡናዋም ግሩም ነው " አለችው አግድም በቁንጥ እያየችው፤ አስተያየቷ ትዝብት ያዘለ ነበር ።

" ምንም አትል ምስጋናውን ለሷ ስጫት " አላት የዝምታው ኬላ በመሰበሩ ደስ ብሎት ፈገግታ በፊቱ ላይ እያንሠራራ ፤

" ሲያዩዋትም የደስ ደስ ያላት ልጅ ናት ከወዴት አገኘሃት "

" ደስ ትበል አትበል አላውቅም ያመጡልኝ የግቢዬ ዘበኛ ናቸው "

" ነገሩስ ላያት ቆንጆ ልጅ ናት "

CamScanner

" ከሌላው ቀን ዛሬ እንዴት ውበትዋ ሊከሰትልሽ ቻለ "

" እኔ እንጃ ዛሬ ነው በደንብ ያየኋት "

ሌላ ተጨማሪ ጥያቄና ሀሳብ ሳይሰነዝር አጐንብሶ መብላቱን ቀጠለ ። ታየች አባ ጨፍቅም ወርቅ ባዘሉ ጣቶችዋ ለምለሙን እንጀራ እየደባበሰች ነገር ታሰላስል ነበር ።

" ልውሰዳትና ሌላ ሠራተኛ ላምጣልህ አለችው"

" ለምን" አላት አባባልዋ አስደነገጠውና

" እዚህ ተርመጥምጣ ከምትሰጠው አገልግሎት የበለጠ መሥራት ትችላለች ፤ ራሷንም በተሻለ ሁኔታ ትጠቅማለች ። እኔ ደግሞ በሷ ምትክ ፈረንጅ ቤት ስትሠራ የኖረች ስልጡን ገረድ አመጣልሀለሁ"

" ምን ነካሽ ታየች ፤ መጀመሪያ ነገር በኔ ፍቃድና ትእዛዝ ከቦታ ቦታ የማለዋውጣት የግል እቃዬ አይደለችም ። ሌላው ነገር ልጅቷ ተማሪ ናት ፤ እንደምንም ትምህርትዋን ጨርሳ ከሴትኛ አዳሪነት የተሻለ ሕይወት እንድትይዝ ይህን ሀሳብ ባትደነቅሪባት ደህና መሰለኝ " አነጋገሩ ከረር አለ ።

" መማርዋን እደግፈዋለሁ ። እንድትማርም አደርጋለሁ ። ተምራ በቆጠረችው ክፍል ሳቢያ ግን ያልፍላታል የምትለውን ባዶ ተስፋ አልቀበልም አላምንበትምም ። ዘዴውን ካወቀችበት ከማንኛዋም የቢሮ ሠራተኛ ኑሮ በላይ ጥሪት ቋጥራና አምራ ተዝናንታ ትኖራለች ። ሁሉም እጇን አለስልሶ የቢሮ ሠራተኛ ለመሆን እጅግ የተትረፈረፈ ውድ

ድር ውስጥ ስላለ በዚህ መስክ እድሉ ጠባብ ነው ። ሌላ የኑሮ አማራጭ መፍጠር ብልህነት ነው"

" እና ሴትኛ አዳሪነት ሌላውና የተሻለው አማራጭ የሥራ ዘርፍ መሆኑ ነው ፤"

" በኔ በኩል አዎ ፤ ቡና ቤቱ ሕጋዊ ቀረጥ እንደሚከፍል ታውቃለህ ፤ ሥራ ሆኖ ታምኖበት መሰለኝ ። መጠጥ በመሸጫና ማስተናገጃ ሥፍራ ምን ተግባራት እንደሚከናወኑ እውቅ ነው እኢህም አልታገዱም ። አንተን የመሰሉ የበሰሉ በርቲታ ምሁራን ፤ የቤተሰብም ሆነ የህብረተሰብ ኃላፊዎች እናስተናግዳለን ። የምናበረክተውን ግልጋሎት ንቃችሁ ጠልታችሁንም ስትቀሩ አላየንም ። ቀን ቀን ያወገዘን ሁሉ እንዳወገዘን አይቀርም ። ተቺውም ሰዳቢውም ምላሱን አጥፎ ውጦ ፤ አንገቱን አቅለስልሶ ጨለማን ተገን አድርጎ ከኛ ጉያ አይወጣም ። ኑሮአችን ሥራችን የሚነቀፈውን ያህል ጠቀሜታው ቢገፋ ኖሮ የኔ ቢጤዎች ቁጥር አይበራከትም ነበር ። ለማንኛውም ግንኙነታችሁ ከአውሬና ሠሪነት የዘለለ ካልሆነ ጠቅማኝ እንድትጠቀም እንድወስዳት ፍቀድልኝ "

" ምን ማለትሽ ነው"

" አባባሌ ግልጽ መሰለኝ ፤ ውበት አድናቂ ነህ ውበት ባለበት ሁሉ መገኘት ትወዳለህ ፤ ምናልባት ግንኙነታችሁ ጥልቀት ከሌለው ማለቴ ነው"

" እኔ ነገርሽ ግልጽ ሊሆንልኝ አልቻለም "

" ታሾፋለህ መሰለኝ ። በቡትቶዋ ሥር የተደበቀው ውበትዋ ቢገለጥ ብዙ ታተርፋለች ። ቅርጽዋ ቁመናዋ ሰውነት ቢደረብበት ልዩ ነው ፤ መልኳም ልቅም ያለች

ቆንጆ ናት ። መክሳትዋ ራስዋን በሥርዓት ያለመጠበቅዋ
እንጂ የምትታለፍ ዓይነት አይደለችም ።”

“ ለኔ ከሠራተኛነትዋ ሌላ ምንም ዓይነት ግንኙነት
የላትም ። ይህን ማሰብሽ ይልቅ ለኔ ትልቅ ስድብ ነው”

“ ችግር የጋረደውን ውበት ትመለከተዋለህ የሚል
ግምት ስላለኝ ነው”

“ ከማንም ቆሻሻ ገረድ ጋር የምዋደቅ አድርገሽ
ስለገመትሽኝ አዝናለሁ ”

“ መቆሸሽ ኃጢአት አይደለም የእድል ጉዳይ ነው ።
አንዳንዴም አንተም እንደ ምትለው ፍትህ በነጠፈበት አስ
ተዳደር ተሰንክሎ የመቅረት ዕጣ ይሆናል ”

“ ለማንኛውም እሺ ካለችሽ እሷኑ ጠይቂያት ”

ይህን ሁሉ ንግግር ሲያደርጉ ውዴ ቡናዋን በጓሮ
በኩል ይዛ ወጥታ እየወቀጠች ነበር ። ውብሸት እንዳይ
ላሉ በአባባልዋ እየተናደደ ያለ ፍላጐቱ አከታትሎ ሲጐ
ርስ ፤ ታየች አባ ጨፍቅ ጣቶችዋን በእንጀራው ጀርባ
ጠራርጋ ውዴ ወዳለችበት ሥፍራ በወጥ ቤቱ
በኩል አልፋ ወደ ጓሮ ወጣች ። ያሰበችውን ሁሉ እያሳሳ
ቀች ፤ እየደባበሰች ለውዴ ነገረቻት ። ውዴም በነገሩ ደን
ግጣ ፤ ሀሳቡን ለእናትዋ ነግራ ፤ የሚፈቅድላት መሆን አለ
መሆኑን እንደምትነግራት ገለጸችላት ። የእናትዋን ፈቃድ
መጠየቁ አስፈላጊ እንደማይሆን በግልጽ ለመናገር ባት
ደፍርም በዘዴ በዘዴ በምናብ እንድታየው በፈጠረችላት
አዲስ ሕይወት ጠቃሚታ አንጻር ለፈቃዱ ቦታ እንዳትሰ
ጠው አስገነዘበቻት ። በዚያው እለት ቤትዋን እንድታየው
ያቀረበችላትን ጥሪ ውዴ ሳትቀበለው ቀረች ። ቤትዋንም

ለማየት ከእናቷ የምትሰማውንም መልስ ለመንገር በቀጠ
ሮ ተለያዩ ።

ገበታው ከፍ ካለ በኋላ ታየች አባ ጨፍቅና ውብ
ሽት እንዳይላሉ እንደመጀመሪያው ሁኔታቸው ባይሆንም
እየተጨዋወቱ ረጋ ብለው ጠጡ ። ጊዜው ዘጠኝ ሰዓት
መሆኑን አየ ። የመቅበጥበጥና የመረበሽ ስሜት ይነበብ
በት ጀመር ። የታየች ፈገግታም በቅሬታ ወይቧል ። ሁለ
ተኛውን ቡና ፉት ብላ ካስቀመጠች በኋላ ለመሄድ ተነ
ሳች ። እንድትቆይ ሊለምናት ወይም እንደወትሮው ሊያ
ስገድዳት አልሞከረም ። ሕሊናው ውስጥ ያለው ሀሳብ
እንደመርግ ተጭኖታል ። ሊናገርም ፈልጐ ድምጹ ከጉ
ሮሮው ተወትፎ ሊወጣለት አልቻለም ። እንደ ተለጐመ
ተነስቶ ወደ መኝታ ክፍሉ ገባ ። ውዴም ተነስታ ከግድ
ግዳው ልጥፍ ብላ ታየችንና የደነቀረችባትን ሀሳብ ጐን
ለጐን እያየች ቆመች ። ታየች አባ ጨፍቅ የሳሎኑን በር
ከፍታ በዝግታ ወደ በረንዳው ስትወጣ ውዴ በትህትና
ለጥ ብላ እጅ ነሳቻት ። ታየችም በርኅራኄ ዓይን አየቻት ።

ከመኝታ ክፍሉ ሲመለስ ረጅም አፍንጫውን እያ
ሻሸ ተከትሏት ወጣ ። የዳመነ ፈገግታ የተላበሰውን ፊቷን
ወደሱ አቅንታ እንዲጨብጣት እጅዋን ዘረጋችለት ። የለ
ሰለሱና የወርቅ እንክብል ያዘሉ ጣቶቿን በሁለት እጆቹ
መካከል አስገብቶ ዳሰሳቸው ። ወዲያውም የተጣጠፈ ወረ
ቀት ቢጤ ነገር አስጨበጣት ። ጐንበስ ብላ አየችው ።አንድ
የመቶና አንድ የሃምሣ ብር ኖቶች ነበሩ ። ስሜቱ ግልጽ
ባልሆነ አስተያየት ቀና ብላ ተመለከተችው ።

“ ምርጫሽን ባለማወቄ ገዝቼ ላመጣልሽ አልቻል
ኩም ታየች የኔ እመቤት ሽቶ ግዥበት ” አላት እንደመለ
ማመጥ እየቃጣው ። ብሮቹን ጠቅልላ እንደ ሲጋራ በጣ
ቶችዋ መካከል ይዛ እጅግም ሳትደነቅ አመሰገነችው ።

ተሰናብታው ስትሄድ እሷንም ሊሸኛት አልፈቀደም ።በረንዳው ላይ ተሰናብቷት ወደ ቤቱ ገባ ። ታየች አባ ጨፍቅም እየተውረገረገች የሽቶዋ መዓዛ የአካባቢውን አየር እያወደ ወደ መኪናዋ አመራች ።

ተመልሶ ገብቶ በሳሎኑ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ ተንቆራጠጠ ። ውዶ የቡና እቃዋን ለቃቅማ ወደ ወጥ ቤትዋ በመሄድዋ እንጂ ሶስተኛውን ቡና መጠጣት አሰኝቶት ነበር ። ብስጭትጭት አደረገው ። ብቻውን ያናግረው ጀመር ። “ አይ አዲስ አበባ ” አለ ደጋግሞ ።

“ አይ አዲስ አበባ ፤ ለጋው ለግላጋው እንደ አሸን የፈላባት ፤ ውበት በየዓይነቱ የፈሰሰባት ምድር ፤ የሰው አምሮት በነጋ በጠባ በወሲብ ግለት የሚንጠለጠልባት ጉደኛ ቦታ ፤ መልክ ፤ ቅርጽ ፤ ገላ ፤ አካሄድ ፤ አስተያየት ፤ አለባበስ ፤ አሳሳቅ ፤ በማራኪ ኃይላቸው የሞሉባት የማግኔት ጐተራ፤የሰው እሸት የሚታይባት ፤ የሰው እሸት እንደ አምሮት እንደ ፍላጐት በበጋ በክረምት በቀን በማታ የሚቀመስባት አዚማም አራዳ ፤ መላ ያጣች ውጥንቅጥ ከተማ፤ ሕይወቴንም መላ ያሳጣችው መተተኛ መንደር ” አለ አዲስ አበባንና የማይገታ ፍላጐቱን ጐን ለጐን እያነጻጸረ የእድሜውን ገመናም በጥቂቱ ገልቦ እየተመለከተ ። በእለተ እንቁጣጣሽ ከረፋዱ ጀምሮ የገጠመውን እያሰላሰለ ተናዶ “ ሺት ” አለና በስሱ ተፋ ።

ለጥቂት ጊዜ በዝምታ ኮተንጐራደደ በኋላ ፤ ድንገትከት ብሎ ከልቡ ሳቀ ። “ ሴቶቹን ዛሬ ምን አቅለበለባቸው” አለ በትዝብት ። ሲስቅ የተከደኑ ዓይኖቹ ሲገለጡ በአበቦቹ ላይ እንደ ድንገት አረፉ ። አውጥቶ ሊወረውራቸው አሰኝቶት ሄደና ሲደርስ አሳዘኑት ። እጁን ሰበሰበ ።

ጽጌረዳዎቹን አጐንብሶ አሸተታቸው ። ህሊና መሸሻም በአበቦቹ ውስጥ ታየችው ።

ቃል በቃል የተናገረችውን ሁሉ አስታወሰ ። እንደ በትዋ አዝሎት የነበረው ቅሬታና የመሰበር ስሜት ተሰማው ። በሴት ቅርጿና መልኳ፤በአመለካከትዋ ስፋት በሥራዋና በምግባሯ ብስለት ቢያደንቃትም ሊያፈቅራት ባለመቻሉ አዘነ ። ጥቅም እንጂ ፍቅር ሞቅ ያለ ስሜት ሰጥቶት ባለማወቁም ገረመው ።

ኩሩ ነች አትበገርም ሲባል ሰምቶ ፤ ከጓደኞቹ ተወራርዶ ሊያንበረክካት እንደሚችል ምሎ በተንኮል ጠልፎ ለፍቅር ካጋለጣት በኋላ ስትንገላታ እያየ ሊረዳት አልቻለምና እያዘነ ጠላት ። ሁኔታዋ አበሳጨው ።

“ ሴት ብሎ ነገር ፤ ቢማሩ ባይማሩ ፤ ወጣት ቢሆኑ ቢያረጁ ፤ የተለየ አቋም የማያሳዩ ደካሞች ። ፍቅር ያዘን ካሉ ይሉኝታቸውን አውልቃው ጥለው የሚደናበሩ ንብሶች ። መወትወት የማይሰለቹ ፤ ሙጭጭ ብለው መጣበቅ የሚፈልጉ ህሊና ቢሶች ። ምን ይኳታል እቺ ደግሞ ፍቅር ለምትለው የስሜት ከበሮ መንፈስዋን የወጠረች ከንቱ ” አለ ።

ባትሰማውም ሕሊና መሻሻን አጥላልቶ ሰደባት ። እንደ ልማዱ አፍንጫውን እያሻሸ ነፍሱን መረመራት ። በልቡ የዘራችው አንዳችም የፍቅር ፍሬ እንደሌለ አረጋገጠና ዳግም አይኑን እንዳታየው ሊያደርግ ወሰነ ።

“ ጋሽ ” አለችው በዚያ ቀጭንና ደካማ ድምጿ

“ አቤት ” አላት ቀና ብሎ

“ የሚያዘኝ ሥራ ከሌለ ልሂድ ”

CS CamScanner

" ሥራሽን ከጨረስሽ ሂጂ ፤ ብቻ እንግዳ ከመጣ የሚጠጣ የሚበላ ነገር ማቅረብ እንድችል ግልጽ ቦታ ላይ አቀራርቢልኝ "

" እሺ"

" መጀመሪያ ኮቴን አቀብይኝ" አላት ልትመለስ እንደጀመረች ።

ኮቱን ከመኝታ ክፍል ልታመጣለት ስትሄድ ትዝ አለውና መንፈሱን አሰባስቦ ልብ ብሎ ተመለከታት ። ታዬች አባ ጨፍቅ የተናገረችለትን ውበት በውዴ ቁመና ላይ መፈለግ ጀመረ ። ገና በማደግ ላይ ያለች ጉስቋላ ልጃገረድ እንጂ የተባለውን ሁሉ አልመሰልህ አለችው ።ተመልሳ ስትመጣም ከፊት ለፊቷ በፈጣን ዕይታ ከላይ እስከ ታች ውዴን ገመገማት ። " እውነትም" አለ ። ከመቆሸሸዋ በቀር ።

ኮቱን ተቀብሎ እጁን ወደ ኪሱ እየሰደደ እንደገና ሲያያት ዐይን ለዐይን ተጋጩና የግጭቱ ስሜት ሁለቱንም ሰቀጠጣቸው ። ውዴ አንገቷዋን ደፋች ። ውብሸትም ቀስ ብሎ ፊቱን ወደ ሌላ አቅጣጫ አዞረ ። ወደ ወጥ ቤትዋ ለመመለስ ራመድ ስትል ፤" አንዴ ቆይ " አላትና ቆመች ከኮቱ ኪስ የፈለገውን አውጥቶ መልሳ እንድታስቀምጥ ሰጣት ። በዓይኖቹ እንደገና ተከተላት ። ኮቱን በጥንቃቄ ይዛ ወደ መኝታ ክፍሉ ተመለሰች ። የሚያስላስለውን ጉዳይ ያወቀችበት መስሎት ደንግጧል ። ከተቀመጠበት ተነስቶ እጆቹን እኪሱ ከቶ ቆሞ ጠበቃት ።

ስትመለስ ፤

" ውዴ " አለ

" አቤት "

" ዘንድሮ ስንተኛ ክፍል ትገቢያለሽ "

" ወደ አስረኛ "

" በርትተሻል ፤ ከአሁኑ ጀምረሽ በጥሩ ወጤት

አስራ ሁለተኛን ለማለፍ መሰናዳት ማጥናት አለብሽ

" እሺ"

" ለአዲሱ ክፍልሽ መማሪያ ደብተር መግዥያ ነው" እጁን ዘረጋ ።

" እሺ ጋሽ እግዚአብሔር ይስጥልኝ " ለጥ ብላ እጅ ነሳችው ። ዕንባ ባቀረሩ ዐይኖችዋ ቀና ብላ አይታው ፈገግ ስትል እንደገና ፈገግ ብሎ በደምብ የገጽታዋን ውበት ተመለከተ ።

" ለእናትሽ እንኳን አደረሰዎት ብሏል በያቸው"

" እሺ" አለችው እንዳጐነበሰች ።

ወ/ሮ ሙሉ የውዴ እናት የውዴን ሥራ መስራትና የጉልበት ዋጋ መቀበል ስላልፈቀዱት በመጀመሪያ ብዙ ተከራክረውበት ነበር ። ሰው ጉልበትና ጤና እያለው እንዴት በችግር ይሸነቆጣል ብለው ስለ ተቆጡና ስላሳመኗቸው የአብዬ ቅጣውን ምክር በመቀበል በይበልጥም ቀጣሪው ውብሸት እንዳይላሉ በቤቱ ውስጥ የሚያደክም ሥራ እንደሌለውና ደህና ሊከፍላት እንደሚችል እሳቸውም እንደሚጠብቋት በማስረዳት በጽዳት ሥራ እንድትቀጠር ሲያደርጉ ፤ የውሉ እለት ወ/ሮ ሙሉ አብረው መጥተው ቤቱን አይተው ውብሸትን ተዋውቀዋል ። ብታጠፋ እንዲመክሯት ፤ በተረፈ ግን በጽዳት ሥራውና በታማኝነቷ የማታሳፍራቸው መሆኑን ገልጸው ከተለያዩ በኋላ ፤ውዴ ውብሸት እንዳይላሉ ቤት በጽዳት ሥራ ለአንድ ዓመት

ያህል ሰርታለች ። ምግብ እንድትሠራለት ካደረገ ግን ገና ሶስት ወር ነው ። ደሞዝዋንም ሃያ ብር አድርጐላታል።

ውዴ በጓሮ በኩል ቆልፋ ዘምቢልዋን አንጠልጥላ ሮጠች ። ሃያ ሶስት ቁጥር አውቶቡስን ለግማሽ ሰዓት ሰዓት ያህል ጠብቃ ተሳፍራ አፍንጮ በር አፋፍ ላይ ካለው ፌርማታ ወርዳ ቁልቁል ወደ ቤቷ ገሰገሰች ።

ሁለት መለኪያ ጅኑን አከታትሎ ከጠጣ በኋላ ሙዚቃ ከፍቶ እየሰማ ከሰፊው ሶፋ ላይ ተጋደመ ። አስር ሰዓት ተኩል ላይ ሸማ ተጐናጥፋ አምራ ቷውባ ደረሰችለት ። አበባየሁ ከምንጊዜውም ፈክታ ታየችው ። ተሸቀጥቁጦ ተቀበላት ። ቤት ያፈራውን የበዓሉን መሰናዶ ጉድጉድ ብሎ አቀረበ ።

የዓመት በዓል ሆድ ሆነና ለወጉ ያህል ለካከፈችው እንጂ የቀረበውን አልበላችውም ። የቀራረበውን እቃ ለማ ንሣት ከወጥ ቤት ወደ ሳሎን እየተመላለሰ እንዳለ ስልኩ ጮኸ ። አበባየሁ አነሳች ።

“ ሀሎ ” አቤት ” አለች አበባየሁ ።

“ አለ ። አንድ ጊዜ ይጠብቁ ”

ውብሸትን ጠራችው የሚናገረውን ለመስማት ጆሮ ዋን አስልታ ዞር አለች ። መነጋገሪያውን ተቀብሎ ቲለጥጦ ቆመ ።

“ አልወጣሁም ፤ ሌላ እንግዳ መጣብኝ ”

“ ነገርኩሽ ፤ እንግዳ ስላለብኝ አልወጣም ”

“ አይመለከትሽም ”

“ ጊዜ ያለኝ አይመስለኝም አልመጣም ”

“ ነገም አይመቸኝም ” ዘጋው ። ታየች አባ ጨፍቅ ነበረች ።

አበባየሁ እጇቿን ታጥባ ስትመለስ ሁለት እጆቹን ዘርግቶ ተቀበላት ለስላሳ ከንፈሮቿን ሳማቸው ። አንገ ቷን በጋለ ትንፋሹ ጡቶችዋን በእጆቹ እየዳሰሰ አቀለጣት ግዙፍ ሰውነቷ እየሟሸሸ ሙሉ በሙሉ በእቅፉ ውስጥ ወደቀች እንደምንም መኝታ ክፍል ደረሱ ።